በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
Ministry of Education

**መመሪያ ቁጥር 988/2016 ዓ.ም**

## የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ፈቃድ እና ፈቃድ እድሳት አሰጣጥ መመሪያ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የትምህርት ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ፈቃድ እና ፈቃድ እድሳት አሰጣጥ" መመሪያ ቁጥር 988/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ ቁጥር 515/2014 እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና አዋጅ ቁጥር 954/2008 ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንዳሉ ሆነው በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

**፩) "ፈቃድ የሚሰጥበት ዘርፍ"** ማለት

**ሀ)** በከፍተኛ ትምህርት ለሚሰማራ፣ አጫጭር ስልጠና ለሚሰጥ፣ በከፍተኛ ትምህርት የማማከር

**Directive No. 988/2024 G.C**

## Directive for Higher Education and Technical & Vocational Training Licensing and Renewal of License

In accordance with artcle 19 sub-article 4 of proclamation No. 1263/2021, by the powers and responsibilities of the FDRE executive bodies, the minisetry of education declared this directive.

### Part one
### General provisions

1. ***Short title***

This directive may be cited as "Higher Education and, Technical & Vocational Training Licensing and Renewal of License directive no. 988/2024".

2. ***Definitions***

Notwithstanding the definitions provided in the Higher Education Proclamation No 1152/2019, Council of Ministers' Regulations No. 515/2021 and Technical and Vocational Training Proclamation No 954/2016 unless the context requires otherwise, in this directive:

1) **"Licensing Sector"** shall mean
   a) Granting license for an institutions providing higher education, delivering short term training, engaging consultancy in Higher Education, providing professional competence in Higher Education and delivering program accreditation.
   b) Licesne will be granted to a Technical and Vocational Training institution established by

አገልግሎት የሚሰማራ፣ በከፍተኛ ትምህርት ላይ የሙያ ብቃት ምዘና የሚሰጥ እና የፕሮግራም እውቅና ለሚሰጥ ተቋም ወደ ስራ እንዲሰማራ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፣

**ለ)** በፌደራል መንግስት ወይም በውጭ ሃገር ባለሃብት ወይም በሀገር ዉስጥ በፌደራል ደረጃ ለመሰማራት የተቋቋመ ወይም በውጭ ሃገር ህግ ተቋቁሞ ስልጠና ለሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

፪) **"የፈቃድ ዕድሳት"** ማለት ቀደም ሲል በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም የፈቃድ ጊዜው ሲጠናቀቅ ሥራውን እንዲቀጥል የሚሠጥ ፈቃድ ነው፤

፫) **"ፈቃድ መሰረዝ"** ማለት ማንኛውም ተቋም ወይም ፕሮግራም በተሰጠው ፈቃድ መሰረት መስፈርቱን አጓድሎ ሲገኝና በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ መሰረት ፈቃድ እንዲመልስ ማድርግ ወይም መንጠቅ ነው፤

፬) **"ዝቅተኛ መስፈርቶች"** ማለት ማንኛውም ተቋም ፈቃድ ለማግኘት ሊያሟላቸው የሚጠበቁ ባለስልጣኑ የሚያወጣቸው አነስተኛ የትምህርት ጥራት መለኪያዎች ናቸው፤

፭) **"ደረጃ"** ማለት አንድ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ሰልጣኝ በስራ ቦታ መስራት የሚጠበቅበትን የስራ ውስብስብነት ወይም ክብደት መጠን የተቀመጡ ስራዎችን መሰረት አድርጎ በተቀመጡ ንዑስ የብቃት አሃዶች የሚመደብ ከአንድ እስከ አምስት የተቀመጠ ደረጃ ነው፤

፮) **"የሙያ ደረጃ"** ማለት በስራ አለም በሚገኙ ሙያተኞች የሚዘጋጅ የሙያ ደረጃ ሲሆን ሰዎች በስራ ዓለም ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ሊኖራቸዉ የሚገባ የእውቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት ብቃት የሚያመለክት ነው፤

፯) **"ተስማሚ የማሰልጠኛ ቁሳቁስ"** ማለት ለአካል ጉዳተኛ ሰልጣኞች ተደራሽ ወይም ተስማሚ የሆኑ የስልጠናአካባቢወችንና መሳሪያዎችን የሚያካትት

the fedral government or by foreign investor or an individual to engage at federal level or institution established by a foreign law.

2) **"Renewal of License"** shall mean a permit accorded to an institution which has previously granted license from the authority upon expiration so as to continue service in the sector;

3) **"Cancellation of License"** shall mean return or revoke of license by this directive, made against any institution or program which compromised the criteria set by the authority upon granting of license;

4) **"Minimum standards"** refer to the minimal quality of educational standards set by the authority, that any institution must meet in order to be licensed.

5) **"Level"** shall mean unit of competence which ranges from one up to five granted to any trainer of technical and vocational field to indicate the level of complexity and difficulty of assignments which she/he is supposed to accomplish at his/her respective field of training;

6) **"Occupational Standard"** shall mean professional standard designated for professionals engaged at various duties which indicates the level of knowledge, skills and attitude they are supposed to be equipped with to successfully discharge in their respective fields of assignments;

7) **"Adaptive Training Materials"** shall mean environment and materials addressing persons with disability designed in a manner which is more accessible or suitable to the trainees' needs;

8) **"Regular Education"** shall mean an education program delivered on a regular day time periods.

9) **"Online Learning"** shall mean a system of higher education offered entirely online using internet and ICT materials without the student

ነው፤

፰) **"መደበኛ ትምህርት"** ማለት በቀን ክፍለ ጊዜ የሚሰጥ ትምህርት ነው፤

፱) **"የበይነ-መረብ መስመር ትምህርት(Online learning)"** ማለት ሙሉ በሙሉ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን በመጠቀም በበይነ መረብ አማካኝነት ተማሪ በአካል መገኘት ሳያስፈልገው ባለበት ቦታ ሆኖ ትምህርቱን እንዲከታተል በማድረግ የሚሰጥ የከፍተኛ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ነው፤

፲) **"የርቀት ትምህርት"** ማለት ፈቃድ በተሰጠበት ከተማና አካባቢ እስከ 50 ኪ.ሜ ራዲየስ የሚሸፍን በቦታ የተገደበ ሆኖ ቢያንስ በአንድ ተርም ሁለት(2) ጊዜ ተማሪዎች በአካል እየተገኙ የገጽ ለገጽ ትምህርት የሚሰጥበት የከፍተኛ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ነው፤

፲፩) **"ተከታታይ ትምህርት"** ማለት በማታ፣ በቅዳሜና እሁድ ወይም በክረምት ትምህርት የሚሰጥበት የመርሃ ግብር ነው፤

፲፪) **"የማታ ትምህርት"** ማለት በማታ ክፍለ ጊዜ ትምህርት የሚሰጥበት ዘዴ ሆኖ በዓመት እኩል የተከፋፈሉ ሶስት ሴሚስተሮች ክረምትን ጨምሮ የሚሰጥበት ዘዴ ነው፤

፲፫) **"የሳምንቱ መጨረሻ ትምህርት"** ማለት በሳምንቱ መጨረሻ ቅዳሜና እሁድ ክፍለ ጊዜ የሚሰጥ ሆኖ በዓመት እኩል የተከፋፈሉ ሶስት ሲሚስተሮች ክረምትን ጨምሮ የሚሰጥበት ዘዴ ነው፤

፲፬) **"የክረምት ትምህርት"** ማለት በክረምት ወራት የሚሰጥ የከፍተኛ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ነው፤

፲፭) **"ድንበር ተሻጋሪ"** ማለት ውጭ ሀገር እውቅና ያለው ተቋም ሀገር ውስጥ ከሚገኝ ፈቃድ ወይም እውቅና ካለው ተቋም ጋር በመተባበር ወይም እውቅና ያለው የውጭ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሀገር ውስጥ ፈቃድ በማውጣት የሁለተኛ ዲግሪ እና ሶስተኛ ዲግሪ መርሃ ግብር በጋራ ወይም በተናጠል የሚሰጥበት የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ነው፡፡

being required to physically avail to the institution

10) **"Distance Education"** shall mean a system of higher education limited to covering 50 kms radius from the city or town where institution granted license and where students are given face to face deliberations at least two times per term;

11) **"Continuing education"** shall mean an education given in the evening, weekend, or summer modalities;

12) "**Evening Education**" shall mean an education program delivered at nights from Mondays to Fridays, arranged in three proportionate semesters of each year including the summer season;

13) **"Weekend Education"** shall mean an education program delivered at weekends (Saturdays and Sundays) sessions, arranged in three proportionate semesters of each year including the summer season;

14) **"Summer Education"** shall mean a system of higher education delivered during the summer (Kiremt) season;

15) **"Cross-border Education"** shall mean a system of education wherein a foreign accredited institution delivers in cooperation with locally licensed or accredited institution or a foreign accredited higher education institution which secured license locally to jointly or severally deliver Masters and PhD programs together:

16) **"Campus relocation License request"** shall mean a permit which shall be granted to an institution where such institution which was previously licensed requests to shift to other place in the same city or town when the license was granted upon the authority's confirmation;

17) **"status"** shall mean status granted to higher education institutions such as university,

፲፮) **"ህንፃ ወይም ጊቢ ቅያሬ ፈቃድ"** ማለት አንድ ተቋም ፈቃድ ባገኘበት ከተማ ውስጥ ህንፃ ወይም ግቢ ወደ ሌላ ቦታ ለማድረግ ሲፈልግ በባለስልጣኑ ተገምግሞ ተሰጥቶት የነበረው ፈቃድ እንዲቀጥል የሚሰጥ የፈቃድ አይነት ነው፤

፲፯) **"የደረጃ ስያሜ"** ማለት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጥ የዩኒቨርሲቲ፣ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣ የኮሌጅ እና የኢንስቲትዩት ስያሜ ወይም ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም የሚሰጥ የፖሊቴክኒክ የኮሌጅ፣ የኮሌጅ ወይም የኢንስቲትዩት ደረጃ ስያሜ ነው፤

፲፰) **"አጫጭር ስልጠና"** ማለት ማንኛውም ተቋም የከፍተኛ ትምህርትን ወይም የቴክኒክና ሙያ ስልጠናን ሊያግዝ የሚችል ተጨማሪ እውቀትንና ክህሎትን ለማስተላለፍ የሚሰጥ ማንኛውም ስልጠና ነው፤

፲፱) **"የተማሪ ቅበላ መጠን ጥያቄ"** ማለት ተቋማት ባላቸው የግብዓትና የሰው ሀይል መጠን ለማስተማር የሚፈቀድ የተማሪ ቁጥር ብዛት ጥያቄ ነው፤

፳) **"ፕሮግራም ማስፋፊያ ጥያቄ"** ማለት ማንኛውም ተቋም ቀድሞ ፈቃድ ባገኘበት ፕሮግራም በተፈቀደለት የተማሪ ቁጥር ላይ ተጨማሪ ተማሪዎችን ለመቀበል በመስፈርቱ መሰረት ተጨማሪ የግብዓት እና የሰው ሃይል ተሟልቶ የሚቀርብ ጥያቄ ነው፡፡

፳፩) **"ተጨማሪ ካምፓስ ጥያቄ"** ማለት ማንኛውም ተቋም ቀደም ብሎ ፈቃድ ካገኘበት ካምፓስ ውጪ አዲስ ካምፓስ ለመክፈት የሚቀርብ ጥያቄ ነው፤

፳፪) **"ተጨማሪ ፕሮግራም ጥያቄ"** ማለት ማንኛውም ተቋም ፈቃድ ካገኘበት ፕሮግራም ዉጪ ሌላ አዲስ ተጨማሪ ፕሮግራም ለመክፈት የሚቀርብ ጥያቄ ነው፤

፳፫) **«ሰው»** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፬) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፤

university college, college and institute or to technical and vocational colleges such as Polytechnic College, College or institute level

18) **"Short Term Training"** shall mean any kind of training given at Higher Education or Technical and Vocational Training program for capacity building or for in parting knowledge and skills;
19) **"Student admission Capacity"** shall mean the maximum number of students institutions can accommodate inline with the in puts and human resource;
20) **"Program Expansion request"** shall mean when an institution shall fulfil additional input and human resources to admit additional students on the Same existing and previously licensed program;
21) **"Additional Campus Request"** shall mean a request made by an institution to open new campus in addition to previously licensed campus;
22) **"Additional Program request"** shall mean a request made by an institution to open a new program in addition to the ones Licensed was already granted;
23) **"Person"** shall mean any natural person or an organ with legal personality.
24) Any expressions in masculine shall include feminine expression as well.

### 3. *Scope of Application*

This directive shall apply on any higher education and on private or public Technical and Vocational Training institutions license granted by the authority.

## *Part two*

## *Fundamental Affairs for Institutions, Programs, Teachers and Students*

### 4. *Fundamental Affairs for Institutions*

1) The institution shall be established on objectives

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት እና በባለስልጣኑ ፈቃድ የሚያገኙ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ በተሰማሩ የመንግስት እና የግል ተቋማት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የተቋም፣ የፕሮግራም፣ የመምህራን እና የተማሪ መሰረታዊ ጉዳዮች

### ፩. የተቋም መሰረታዊ ጉዳዮች

፩) የሚቋቋመው ተቋም ሀገራዊና ሕዝባዊ ፍላጎቶችን ማዕከል ያደረገ ራዕይ፣ ተልእኮና አላማ ሊኖረው ይገባል፤

፪) ተቋሙ በአክሲዮን ወይም በግል (ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር) የሚቋቋም ከሆነ ስልጣን ባለው አካል የጸደቀ የመመስረቻ ጽሁፍና የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም የተቋሙ የህጋዊ ባለቤትነት ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፫) ማንኛውም በከፍተኛ ትምህርት ለመሰማራት የሚፈልግ አዲስ ወይም በስራ ላይ ያለ የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከስራው እና ከተማሪዎች ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጉዳዮች ሊውል የሚችል የስራ ዋስትና ብር አምስት መቶ ሺ (500000) ወይም ተመጣጣኝ ዋስትና ማስያዝ ይኖርበታል፡፡

፬) ማንኛውም ተቋም በማንኛውም መርሃ ግብር ትምህርት ለማስተማር ወይም ስልጠና ለመስጠት በባለስልጣኑ ተገምግሞ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤

፭) ማንኛዉም የሀገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወይም ከወጭ ሀገር በመምጣት በድንበር ተሻጋሪ መርሃ-ግብር ለማስተማር በዉጭ ሀገር ያለዉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በጠየቀው ፕሮግራም እዉቅና ያለው ሊሆን ይገባል፣ እንዲሁም ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ሞዴሎች በመምረጥ ማመልከቻ ሲያቀርብ በወጣው መስፈርት መሰረት የሚገመገም ይሆናል፡፡

addressing national and public interests;

2) Where the institution is established as a share company or a private (Private Limited Company), it shall have article of association and memorandum of association duly approved by the concerned authorities and documents stating the legal ownership of the institution shall be provided;

3) Any existing or new company which seeks to involve in the higher education sector shall attach a guarantee of birr 500000 (Five hundred thousand birr) or unconditional bank guarantee to ensure that issues related to the students and the activity will not be compromised;

4) Any institution shall be evaluated and get a license by the authority to teach or offer training in any program.

5) For any local higher education institution or a foreign institution request following the listed models to launch a Cross border higher education, the foreign institution shall have accreditation in the requested program;

a) Can apply for a Branch Campus Model, A recognized foreign higher education institution that wants to provide education in a cross-border program in second degree and third degree can open a branch campus in Ethiopia and provide education in Ethiopia in an equivalent manner in the subjects recognized in the country.

b) Can apply for a Franchised Model at the second-degree level in which an institution in one country provides education in accordance with an agreement that allows it to use the name and reputation of a recognized higher education institution in another country.

c) Can apply for a twinning Model, in which a

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ሀ) የቅርንጫፍ ካምፓስ ሞዴል (Branch campus model) ማመልከት ሲፈልግ በሁለተኛ ዲግሪና ሶስተኛ ድግሪ በድንበር ተሻጋሪ መርሃ-ግብር ትምህርት መስጠት የፈለገ እውቅና ያለው የውጭ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የቅርንጫፍ ካምፓስ (Branch Campus Model) ኢትዮጵያ ውስጥ በመክፈት በሃገሩ እውቅና ባገኘባቸው የትምህርት ዓይነቶች በአቻ መልኩ ኢትዮጵያ ውስጥ ትምህርት የሚሰጥበት አግባብ ነው፤

ለ) "ፍራንቻይዝድ ሞዴል (Franchised Model) ማመልከት ሲፈልግ በሁለተኛ ዲግሪ ወይም በሶስተኛ ድግሪ በድንበር ተሻጋሪ መርሃ-ግብር ሀገር ውስጥ የሚገኝ ተቋም ውጭ ሀገር ከሚገኝ እውቅና ያለው እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋምን ስምና ታዋቂነቱን መጠቀም የሚያችለውን ስምምነት ተከትሎ ትምህርት የሚሰጥበት አግባብ ነው፤

ሐ) በመንትያ ሞዴል (Twining Model) ማመልከት ሲፈልግ እውቅና ያለው የውጭ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ኢትዮጵያ ውስጥ ፈቃድ ወይም እውቅና ካለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ጋር በጋራ ትምህርት የሚሰጡበት፣ ስርአተ ትምህርት የሚከልሱበት፣ የውጭ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን ኢትዮጵያ ውስጥ በመምጣት ወይም በቴክኖሎጂ በመታገዝ ትምህርት የሚሰጡበት፣ ፈተና የሚፈትኑበት እንዲሁም ተማሪዎቹ ውጭ አገር በሚገኘው የውጭ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በመሄድ ለሁለተኛ ዲግሪ ቢያንስ ለአንድ ሴሚስተር ወይም ከአንድ ዓመት ላልበለጠ የትምህርት ጊዜ ወይም የዶክትሬት ዲግሪ ሲሆን ለሁለት ሴሚስተሮች ትምህርታቸውን ውጭ አገር ባለው ተቋም የሚከታተሉበት የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ነው፤

መ) "የበይነ-መረብ መስመር ትምህርት(Online learning) ሞዴል" ለመስጠት ማመልከት ሲፈልግ በዚህ መመሪያ ዉስጥ ያለው ትርጓሜ እንዳለ ሆና በበይነ-መረብ እና በትምህርት መስኩ እውቅና ያለው የውጭ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ፈቃድ ካለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ጋር በጋራ የሚሰጥ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ነው፡፡

፮) በሀገር ውስጥ ማንኛዉም በድንበር ተሻጋሪ

recognized foreign institution of higher education in Ethiopia with a licensed or recognized institution of higher education in which they teach together, review the curriculum, teach foreign higher education institution teachers in Ethiopia or with the help of technology, conduct exams, and It is a method of education where the students go to a foreign institution of higher education for at least one semester for a master's degree or for a period of more than one year or for a doctorate degree and follow their education for two semesters in an institution abroad;

d) Can apply for an Online Learning Model, when the definition given in this directive, it is a system of education whereby an accredited foreign online teaching higher education institution may jointly deliver programs with a locally licensed higher education institution.

6) For any local higher education institution to launch Cross border higher education, the institution shall have similar educational delivery system which is equivalent to its foreign counterpart institution;

7) Any institution Seeking to be engaged in education and training sector shall have Business registration and business license or investment license from the concerned authority in charge of issuing permits to involve in the sector;

8) Any Institution may grant status upon its application or during their establishment, or after granted a license or while they are on active service thereafter;

A. "Institute will be granted

i. A status granted to a higher education institution which has been offering degree program at least in one subject according to provisions of Article 13 of the Higher Education Proclamation No. 1152/2019 and upon fulfillment of detailed standard set forth by the authority;

Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

መርሃ-ግብር ለማስተማር የሚፈልግ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከዉጭ ሀገር ካለዉ ተቋም ጋር አቻ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ መስጠት ይኖርበታል፤

፯) በትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ተቋም ስልጣን ባለው አካል በትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስችለው የንግድ ምዝገባ ፈቃድ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፤

፰) ተቋማት የደረጃ ስያሜ የሚሰጣቸው በሚቋቋሙበት ጊዜ ወይም የመጀመሪያ ፈቃድ በሚሰጣቸው ወቅት ወይም ፈቃድ ተሰጥቷቸው በሥራ ላይ እያሉ የደረጃ ስያሜ ጥያቄ ሲያቀርቡ እና መስፈርቱን ሲያሟሉ ሆኖ ቀጥሎ ባሉት ደረጃ ስያሜ መሰረት ይሆናል፤

**ሀ)** ኢንስቲትዩት ደረጃ ስያሜ የሚሰጠው

1. የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 13 መሰረት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቢያንስ በአንድ የትምህርት አይነት በዲግሪ ፕሮግራም ትምህርት መስጠት የሚችል እና ባለስልጣኑ የሚያወጣቸውን ዝርዝር መስፈቶች ሲያሟላ የሚሰጥ ስያሜ ነው፤
2. የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ በደረጃ 1 እና 2 ላይ የሚመደቡ የሙያ መስኮችን በማካተት አጫጭር ስልጠናን ጨምሮ ትምህርትና ስልጠና ለሚሰጥ ተቋም የሚሰጥ ስያሜ ነው፤

**ለ)** ኮሌጅ ደረጃ ስያሜ የሚሰጠው

የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 13 መሰረት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆነ አንድ የትምህርት ክፍል በዲግሪ ፕሮግራም ትምህርት የሚሰጥ እና ባለስልጣኑ የሚያወጣቸውን ዝርዝር መስፈቶች ሲያሟላ የሚሰጥ ስያሜ ነው፤

ii. A status granted to a technical and vocational institution offering level I and level II education and training as well as short-term trainings.

**B.** College will begranted when:

i. A status granted to a higher education institution which has been offering degree program in an institution set up in a unit above department according to provisions of Article 13 of the Higher Education Proclamation No. 1152/2019 and upon fulfillment of detailed standard set forth by the authority;

ii. A status granted to a technical and vocational institution offering from level I and level IV on disciplines designated for such level of education and training.

C. University College status granted to institution that fulfills criteria set forth in provisions of Article 11 sub-articles 1-3 of the Higher Education Proclamation No. 1152/2019 and the detailed standard set forth by the authority;

D. "Polytechnic College" shall mean an education and training institute which undertakes professional disciplines which fall under level I-V of the Technical and Vocational Sector;

E. "University" shall mean an institution which fulfills the standard set forth pursuant to education Article 10 sub-articles 1-3 of the Higher Education Proclamation No. 1152/2019 and the detailed criteria set forth by the authority

9) Any institution submits a request for a license in

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ ከደረጃ 1 እስከ 4 ላይ የሚመደቡ የሙያ መስኮችን በማካተት ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ ተቋም ነው፤

ሐ) ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃ ስያሜ የሚሰጠው በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 11 መሰረት ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ እንዲሁም ባለስልጣኑ የሚያወጣቸውን ዝርዝር መስፈቶች ሲያሟላ የሚሰጥ ስያሜ ነው፤

መ) ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ደረጃ ስያሜ የሚሰጠው በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ ከደረጃ ከ1 እስከ 5 ላይ የሚመደቡ የሙያ መስኮችን በማካተት ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ ተቋም ነው፤

ሠ) ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ስያሜ የሚሰጠው በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 10 መሰረት ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ እንዲሁም ባለስልጣኑ የሚያወጣቸውን ዝርዝር መስፈርቶች ሲያሟላ የሚሰጥ ስያሜ ነው፤

፱) ማንኛውም ተቋም በአዲስ የትምህርት መስክ ፈቃድ ጥያቄ ሲያቀርብ የተማሪ ቅበላ መጠን ፍላጎት አብሮ ማሳወቅ ይኖርበታ፣ ካለው አደረጃጀትና ግብአት አንጻር የሚኖረውን የቅበላ ፍላጎቱንና አቅሙን የሚያሳይ ማስረጃ አብሮ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፲) ማንኛውም ተቋም በማንኛውም የትምህርት መስክ ፈቃድ ካገኘ በኃላ የፕሮግራም ማስፋፊያ ጥያቄ በመጠየቅና ባለስልጣኑ ያወጣውን መስፈርት በማሟላት የተማሪ ቅበላ መጠን ማሳደግ ይችላል፤

፲፩) በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ፈቃድ አግኝተው የሚሰሩ ተቋማት ፈቃድ ባገኙበት የትምህርት መስክ ትምህርቱን ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ አጫጭር ስልጠና መስጠት የሚችሉ ሆኖ

a new field of study, it shall also notify the student intake capacity along with an application letter; In terms of the existing organization and resources, and Institutions shall be providing evidence of their need and intake capacity of students.

10) Any institution may expand its Intake capacity of students upon a request submitted to the authority and upon fulfilling the criteria so listed, once it has granted license to deliver education or training programs;

11) Any institution Licensed to undertake higher education may offer short term trainings relevant to support the education program it has been to take part; meanwhile, the institution shall obey the level of certificate, length of time and credit hours accepted by standard and guidelines;

12) Any Higher Education institution shall make request, fulfill the criteria set forth by the authority and get license to offer short term training in any field to which license has not been granted; Short-term training provided by any higher education institution, however, shouldn't cause disruption to the institution's regular teaching and learning activities.

13) Any institution shall get a license from the authority to offer consultancy, professional competency evaluation and program accreditation service at higher education sector;

14) An institution which has been imposed penalty may apply for license as the penalty period lapsed;

15) Notwithstanding their professional independence of autonomous institutions involved in teaching learning process, they shall implement their programs by duly observing the requirements made pertaining to quality education, internal organization and intake capacity of their

በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሰረት የሰርተፊኬት ደረጃዎች፣ የጊዜ ርዝማኔ እና የክሬዲት አወር መጠን ጠብቀው መስራት ይኖርባቸዋል፤

፲፪) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ፈቃድ ባላገኙበት የትምህርት መስክ አጫጭር ስልጠና ለመስጠት ፈቃድ መጠየቅ እና ባለስልጣኑ የሚያወጣቸውን መስፈርት ማሟላት ይኖርበታል፤ ይሁን እንጂ በማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጡ አጫጭር ስልጠናዎች የተቋሙን መደበኛ የመማር ማስተማር ሥራ የሚያስተጓጉሉ ሊሆኑ አይገባም፡፡

፲፫) ማንኛውም ተቋም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ለማማከር፣ የሙያ ብቃት ምዘና እና የፕሮግራም እውቅና ለመስጠት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤

፲፬) ቅጣት የተጣለበት ተቋም የቅጣት ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ፈቃድ ሊጠይቅ ይችላል፤

፲፭) ራስ ገዝ ተቋማት የመማር ማስተማር ሂደታቸውን ሲተገብሩ የአሰራር ነጻነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ጥራትን፤ የተቋሙን ዉስጣዊ አደረጃጀት እና የፕሮግራምየመቀበል አቅምን ከግምት ባስገባ መልኩ መተግበር ይኖርባቸዋል፤

፲፮) ማንኛውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለከፍተኛ ትምህርት አግልግሎት የሚውል ራሱን የቻለ አደረጃጀት፣ ግብዓት እና የመማሪያ ህንፃ ወይም ግቢ ሊኖረው ይገባል፤

፲፯) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለከፍተኛ ትምህርት የሚጠቀምባቸውን ግብዓቶች ባለስልጣኑ ከፈቀደለት አገልግሎት ውጪ ለሌላ አገልግሎት ማዋል የለበትም፤ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ፈቃድ ካገኘ ተቋሙ ግብዓቶቹን ለቴክኒክና ሙያ፣ ለአጠቃላይ ትምህርት እና ለሌሎች አገልግሎት ሊያወል አይገባም፤

፲፰) ማንኛውም ተቋም ወቅታዊ ተቋማዊ ለውጦችን የሚያንፀባርቅ እና የተቋሙን ወቅታዊ ደረጃ የሚያሳይ ግልጽ እና አስተማማኝ መረጃ

programs;

16) Any higher education institution shall have independent organizational set up, inputs and building or campus dedicated to run higher education service;

17) Any higher education institution granted license to undertake higher education shall not use inputs meant contrary to the objectives including for technical and vocational training, general education and other similar purposes;

18) Any institution must have a standard website with clear and reliable information that reflects current institutional changes and reflects the institution's current status, as well as a video/moving image visible to the public.

19) Institutions shall post the granted license from the authority and admission criteria on the official webpage of the institutions as well as on notice board of the campus where by the service recipients can easily access;

20) Any higher education institution shall have research article of its PhD candidates published on a reputable journal as a requirement for graduation. Details of the criteria shall be issued by the authority;

21) Any higher education institution shall avail copy of the research article or thesis of its graduate students on a national repository (archive) as a requirement for graduation at post graduate level; Details of the criteria shall be issued by the authority;

22) Any institution may amend or improve its organizational structure; and such amendment or improvement shall be reported to the authority;

23) Any institution shall report employment and promotion which applies to its academic, administrative and finance employees to the

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ያለው እንዲሁም ለህዝብ የሚታይ የቪዲዮ/ተንቀሳቃሽ ምስል ያለበት ደረጃውን የጠበቀ ድረ-ገጽ ሊኖረው ይገባል።

፲፱) ተቋማት ከባለስልጣኑ ያገኙትን ፈቃድ እና የመመዝገቢያ መስፈርቶች በተቋሙ ድረ-ገፅ ላይ እና በካምፓሱ ለተገልጋዮች ሊታይ በሚችል ግልጽ በሆነ ቦታ ሊለጥፉና ሊያሳውቁ ይገባል፤

፳) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት ለማስመረቅ የእያንዳንዱ ተማሪ ጥናታዊ ጹሁፍ ወይም አርቲክል ታዋቂ ጆርናል ላይ ሊታተም ይገባል። አተገባበሩ ባለስልጣኑ በሚያወጣው ዝርዝር መስፈርት መሰረት ይሆናል፤

፳፩) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በድህረ ምረቃ ትምህርት ለማስመረቅ የእያንዳንዱ ተማሪ ጥናታዊ ጹሁፍ ወይም አርቲክል በሃገር ደረጃ ሊታተም እና ሪፖሲተሪ ወይም አርካይቭ ላይ ሊቀመጥ ይገባል፣ አተገባበሩ ባለስልጣኑ በሚያወጣው ዝርዝር የአሰራር ስርዓትና መስፈርት መሰረት ይሆናል፤

፳፪) ማንኛውም ተቋም በአደረጃጀቱ ላይ በየጊዜው ለውጦችን ወይም መሻሻሎችን ሊያደርግ ይችላል። የአደረጃጀት ለውጥ ወይም መሻሻል ሲያደርግ ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፤

፳፫) ማንኛውም ተቋም በአደረጃጀቱ መሰረት የአካዳሚክ፣ የአስተዳደርና ፋይናንስ ሰራተኞችን የቅጥርና የደረጃ እድገት መመዘኛዎችን እና አተገባበራቸውን ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፤

፳፬) ማንኛዉም ተቋም የንግድ ስም ስያሜ ሲቀይር ከሚመለከተው ወይም ስልጣን ባለው አካል የተሰጠው አዲስ የስም ስያሜ ማስረጃ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፳፭) ማንኛውም ተቋም የፈቃድ እና የፈቃድ እድሳት አሰራር ላይ ጥያቄ ሲኖረው ለባለስልጣኑ ማመልከቻ በማቅረብና በአካል በመቅረብ ከፈቃድ

authority,

24) Whenever legal trade name of institutions is changed, it shall submit document related to the change to the authority which are issued by the concerned body;

25) Whenever it's necessary the authority may offer professional assistance and clarification in regarding to license and renewal of license criteria;

26) The authority may re-evaluate the licensed programs or granted status, Make some amendments thereto at any time where believes that is necessary,

27) In every aspect of institutional operations, any new or existing institution shall take into account citizens with special need.

28) Any higher education institution shall have at least 25 percent of its current graduates pass exit exam, as a criteria to get renewal of license; It will be applied to the students who will be accepted from the year the country's exit exam began to be given,

29) Any technical and vocational training institution shall have at least 50 percent of current students completing the training pass professional competence examination, as a criteria to get renewal of license;

30) Any technical and vocational training institution may consider training on evening program in consultation with sectoral or public service offices having closer ties with the profession, taking into account suitability, relevance and quality of the training.

31) Any licensed technical and vocational training institution shall support, train and other professionally augment small and micro enterprises;

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ክፍል እንደ አስፈላጊነቱ ከባለስልጣኑ ማብራሪያና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጠዋል፣

፴፯) ባለስልጣኑ በሰጠው ፈቃድ እና የደረጃ ስያሜ ላይ በተለያዩ ምክንያቶች ለውጥ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በማንኛውም ወቅት ተቋማቱን እና ፕሮግራሞቻቸውን እንደገና ሊገመግም እና ማሻሻያ ሊያደርግ ይችላል፤

፴፰) ማንኛውም አዲስም ሆነ ነባር ተቋም በማንኛውም ተቋማዊ ትግበራ ወቅት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፤

፴፱) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የፈቃድ እድሳት እንዲታደስለት ትምህርት ካጠናቀቁት ውስጥ የወቅቱ ተመራቂዎቹ ቢያንስ 25 በመቶ የሚሆኑት የመውጫ ምዘናን ማሳለፍ ይኖርበታል፤ በሃገሪቱ የመውጫ ፈተና መሰጠት ከጀመረችበት አመተ ምህረት ጀምሮ የሚቀበሉት ተማሪ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ይሆናል፤

፵) ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም የፈቃድ እድሳት እንዲታደስለት ከወቅቱ የስልጠና አጠናቃቂ ሰልጣኞቹ ውስጥ ቢያንስ 50 በመቶ ተፈታኞች የሚሆኑት የሙያ ምዘናን ማሳለፍ ይኖርበታል፤

፵፩) ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም በሚታው የስልጠና ኘሮግራም ለመስጠት ያለው አመቺነትና ተገቢነት እንዲሁም በስልጠናው ጥራት ላይ የሚኖረውን ተፅህኖ ከግምት በማስገባትና ከሙያው ጋር ቅርብ ቁርኝት ካላቸው የዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ሊያስተናግድ ይችላል፤

፵፪) ፈቃድ አግኝቶ ሲሰራ የቆየ ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ሊደግፍ፣ ሊያሰለጥን እና እና ሌላም ሙያዊ እገዛ ሊያደርግ ይገባል

፵፫) ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም በአካባቢው ካለ ኢንዱስትሪ ጋር የተደረገ

32) Any technical and vocational training institution shall provide memorandum of understanding signed with an industry in the area to provide practical cooperative training related to the program;

33) Any technical and vocational training institution may claim to get license for the next level training, when 50 percent of trainees who were registered for professional competence are proven to have been competent;

34) Any licensed Institutions offering professional competence evaluation shall have academic credentials of examinee authenticated by concerned authority before undertaking competence evaluation;

35) Any program license remains functioning only as long as the license of the institution remains valid;

36) Any institution shall re-invest at least 25 percent of the net income generated from the education sector for the improvement of education;

37) The authority may decide to re-evaluate the field visit when it is convinced that, the previous evaluation for license lacks sufficient information and evidence;

38) With regard to the license guidelines formulated by the authority to ensure the quality of technical and vocational institutions, the authority may its support in connection with licensing by ratifying a memorandum of understanding with regional and city administration;

39) Any institution shall make campus change only on the same town or city with the radius of not more than 10 Kms.

40) Any higher education institution shall conduct its activities as per the focus area and differentiation (institutional mission) set by the authorized body;

41) When any institution that has been providing

Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

ከፕሮግራሙ ጋር ተዛማጅነት ላለው የተግባር የትብብር ስልጠና የሚሰጥበት የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፴፫) ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም የሚቀጥለውን የደረጃ ፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው የመጀመሪያው ዙር ሰልጣኝ ለሙያ ምዘና ከተመዘኑት ሰልጣኞች ውስጥ 50 በመቶ የሚሆኑት ብቁ መሆናቸው ከተረጋገጠ ብቻ ይሆናል

፴፬) ማንኛውም ፈቃድ አግኝቶ የሙያ ምዘና የሚሰጥ ተቋም የሙያ ምዘና የሚሰጧቸውን ተመዛኞች በቅድሚያ የትምህርት ማስረጃዎቻቸውን ትክክለኛነት ስልጣን ባለው አካል ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

፴፭) የማንኛውም ፕሮግራም ፈቃድ አገልግሎት እየሰጠ መቆየት የሚችለው የተቋሙ ፈቃድ አገልግሎት ላይ እስካለ ጊዜ ብቻ ይሆናል፤

፴፮) ማንኛውም ተቋም በትምህርት ሴክተሩ ከሚያገኘው የተጣራ ገቢ ቢያንስ 25 በመቶ መልሶ ለትምህርቱ ሥራ ማሻሻያ ማዋል ይኖርበታል፤

፴፯) ባለስልጣኑ ተቋማት ላቀረቧቸው የፈቃድ እና ፈቃድ እድሳት ጥያቄዎች የመስክ ግምገማ ሂደቱ በቂ መረጃ እና ማስረጃ አልቀረበም ብሎ ሲያምን ግምገማውን በድጋሜ ሊያካሂድ ይችላል፤

፴፰) በባለስልጣኑ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚወጡ የፈቃድ መስፈርቶችን በሚመለከት ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ከፈቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ከክልል እና ከከተማ አስተዳድር ጋር የትብብር መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም እገዛ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፴፱) ማንኛውም ተቋም የቦታ ወይም የህንፃ ቅያሬ ማድረግ የሚችለው ፈቃድ ባገኘበት ከተማ ውስጥ ብቻ ሲሆን በ10 ኪሜ ርቀት ውስጥ መሆን ይኖርበታል።

፵) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ስልጣን

education and training wants a license to launch a new program or new campus or teach another modality, the license will be granted based on the strength of prior performance, and detailed performance will be made in compliance with the criteria

42) program license For public higher education institutions shall be made pursuant to provisions of article 85 of Higher Education Proclamation No. 1152/2019.

5. ***Fundamental Affairs for Program***

1) Any institution seeking to commence a new program or sustain the existing ones shall undertake needs assessment, market analysis and validation workshop with stakeholders prior to the action;
2) Institutional and program license shall be granted to private higher education and technical and vocational training institution when they have fulfilled the standards ;
3) Programs to be launched by public higher education institutions shall meet the standards;
4) A license issued to any institution will apply only for the campus, program and duration which the authority evaluated for;
5) When the authority grants license to any institution, number of students will be limited as per the standard for every modality and program;
6) any Institutions shall give health science and medical program on regular modality only;
7) Any higher education institution shall deliver distance education only at a first-degree level;
8) Any private higher education institution shall not teach teacher education and law sectors;
9) Any technical and vocational training institutes shall not train any training on distance modality;

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ባለው አካል በሚወጡ የተቋማት ተልዕኮና የትኩረት መስክ ልየታ መሰረት ስራውን ማከናወን አለበት፤

፲፩) ትምህርትና ስልጠና ሲሰጥ የቆየ ማንኛውም ተቋም አዲስ ፕሮግራም ለመክፈት ወይም ሌላ ሞዳሊቲ ለማስተማር ፍቃድ ሲጠይቅ ፈቃዱ የሚሰጠው ከዚህ ቀደም በነበረው አፈጻጸም ጥንካሬ ላይ ተመስርቶ ሲሆን ዝርዝር አፈጻጸሙም በዝርዝር መስፈርት ይገለጻል።

፲፪) የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ፈቃድን በተመለከተ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 85 መሰረት የሚታይ ይሆናል።

## ፭. የፕሮግራም መሰረታዊ ጉዳይ

፩) ማንኛውም ተቋም አዲስ ፕሮግራም ለመክፈት ወይም ነባሩን ፕሮግራም ለማስቀጠል የፍላጎት ዳሰሳ፣ የገበያ ጥናት እና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ አውደ ጥናት ማካሄድ ይኖርበታል፤

፪) ለግል የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የተቋምና የፕሮግራም ፈቃድ የሚሰጠው የወጡ መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ ብቻ ይሆናል፤

፫) የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚከፍቷቸው ፕሮግራሞች የወጡ የመመዘኛ መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፤

፬) ለማንኛውም ተቋም የሚሰጥ ፈቃድ የሚያገለግለው በባለስልጣኑ ተገምግሞ ለተፈቀደለት ካምፓስ፣ የትምህርት መስክ እና ጊዜ ብቻ ይሆናል፤

፭) ባለስልጣኑ ለማንኛውም ተቋም ፈቃድ ሲሰጥ በማንኛውም የትምህርት መስክና መርሃ ግብር የተማሪ ቁጥር ገደብ የሚኖረው ይሆናል፤

፮) ማንኛውም ተቋም የጤና እና የህክምና የትምህርት መስኮችን መስጠት የሚችለው

10) Any higher education institutions seeking to get license for Doctor of Medicine and Specialty program shall have its own teaching hospital;

11) Any higher education institutions institutional curriculum approved by the authority shall not change its degree nomenclature and curriculum prior to expiration of the license without the permission of the authority.

12) A higher Education curriculum evaluated and approved by the authority at institution or campus level may apply at other campuses of the same institution unless the license or renewal of license period has already expired/ lapsed;

13) When higher education institutions request the authority to get license to launch any education, the curriculum shall be evaluated and approved prior to field visit;

14) On a special basis when there is no other option to offer the course, the authority may give a permit to the institutions to offer the course on a block-course basis.

## 6. ***Fundamental affairs for Students***

1) Any institution shall admit students for programs to which is granted license only based on admission criteria set by the concerned body;

2) any institutions shall admit students only who's academic credentials have been authenticated by an authorized body,

3) Any institution shall submit the list of registered students of licensed program to the authority within two months after the class has been begun.

4) Any institution shall enroll and teach students only in licensed institution, campus, mode of delivery, level, program or training name, and permitted number of annual student intake capacity;

5) Any institution shall not enroll and teach a

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

በመደበኛ መርሃ ግብር ብቻ ይሆናል፤

፯) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በርቀት ትምህርት መርሃ ግብር ማስተማር የሚችለው በመጀመሪያ ዲግሪ ብቻ ይሆናል፤

፰) ማንኛውም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመምህርነት እና የህግ ትምህርት ዘርፎችን ማስተማር አይችልም፤

፱) ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም የትኛውንም ስልጠና በርቀት መርሃ ግብር ማሰልጠን አይችልም፤

፲) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በህክምና ዶክትሬት እና በስፔሻሊቲ ትምህርት ፈቃድ ለማግኘት ተቋሙ የማስተማሪያ ሆስፒታል ሊኖረው ይገባል፤

፲፩) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ በተቋም ደረጃ የጸደቀ ስርዓተ ትምህርት የፈቃድ ጊዜው ሳያበቃ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ውጪ የስርዓተ ትምህርት እና የዲግሪ ስያሜ ለውጥ ማድረግ አይችልም፤

፲፪) በተቋም ወይም በካምፓስ ደረጃ በለስልጣኑ ተገምግሞ የጸደቀ ስርዓተ ትምህርት የፈቃድ ወይም ፈቃድ እድሳት ጊዜው እስካላበቃ ድረስ በተመሳሳይ ተቋም በሌሎች ካምፓሶች መተግበር ወይም መጠቀም ይችላል፤

፲፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሁሉም የትምህርት መርሃ-ግብሮች ፈቃድ ሲጠይቁ ስርዓተ-ትምህርቱ በባለስልጣኑ ከመስክ ምልከታ በፊት ቀድሞ መገምገም እና ተገቢ ማስተካከያ ተደርጎ መፅደቅ ይኖርበታል፤

፲፬) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በልዩ ሁኔታ ኮርሱን ለመስጠት ሌላ አማራጭ የለም ተብሎ ሲታሰብ ባለስልጣኑ ትምህርቱ በብሎክ ኮርስ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ወይም ሊወስን

student or trainee; before it's granted a license and after the license or renewal of the license period has lapsed;

6) Any institution shall give and notify students grade report of the previous semester and term; before beginning registration for the next semester and term;

7) Any Student who wants to pursue a postgraduate program shall take the graduate admission test and entrance exam based on the procedure set forth by the concerned body;

8) It shall be ensured that students graduating in any program or subject of study have acquired the right skills, attitude, and knowledge that make them fit in joining the respective world of a career after taking the competence examination conducted by the authorized body.

7. ***Fundamental affairs for Academic staffs***

1) Any institution shall meet the requirements for academic staffs or trainers the curriculum requires and the one set by the authority;

2) Any academic staffs teaching at higher education institutions shall have qualification which is one step higher than the level she or he is to teach;

3) Any institution shall have permanent academic staffs whose academic credentials authenticated by the concerned body.

4) Any institution whose permanently academic staffs have been resigned, shall replace new academic staff within two months of the resignation. The credentials and other supporting document of the replaced academic staff shall be evaluated and permitted.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ይችላል፡

**፮. <u>የተማሪ መሰረታዊ ጉዳይ</u>**

፩) ማንኛውም ተቋም ፈቃድ ባገኘባቸው የትምህርት መስኮች ተማሪዎችን መዝግቦ ማስተማር የሚችለው ስልጣን ባለው አካል በሚያወጣው የመግቢያ መስፈርት መሰረት ብቻ መሆን ይኖርበታል፤

፪) ማንኛውም ተቋም የሚመዘግባቸውን ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃዎች ትክክለኛነት ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ ሊሆን ይገባል፤

፫) ማንኛውም ተቋም ፈቃድ ባገኘባቸው የትምህርት መስኮች የመዘገባቸውን ተማሪዎች ሙሉ መረጃ ትምህርት በተጀመረ በሁለት ወር ውስጥ ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማስገባት ይኖርበታል፤

፬) ፈቃድ የተሠጠው ተቋም ተማሪ መዝግቦ ማስተማር የሚችለው ፈቃድ በተሰጠበት ተቋም፣ ካምፓስ፣ የጊዜ ገደብ፣ መርሃ-ግብር፣ ደረጃ፣ የትምህርት ወይም የስልጠና መስክ እና በተፈቀደለት አመታዊ የተማሪ ቅበላ መጠን ብቻ ሊሆን ይገባል፤

፭) ማንኛውም ተቋም ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት እና የፈቃድ ወይም ፈቃድ እድሳት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪ ወይም ሰልጣኝ መመዝገብ እና ማስተማር አይችልም፤

፮) ማንኛውም ተቋም የቀጣዩን ሴሚስተር እና ተርም ምዝገባ ከማካሄዱ በፊት የቀዳሚውን ሴሚስተር እና ተርም ውጤት ለተማሪዎች ማሳወቅ ይኖርበታል፤

፯) በማንኛውም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በድህረ-ምረቃ ደረጃ፣ በየትኛውም የትምህርት መስክ እና መርሃ ግብር መማር የሚፈልጉ ተማሪዎች የመግቢያ ፈተና (Graduate Admission Test) በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሰረት

5) Expatriate academic staff shall have legal residence and work permit as well as authenticated and equivalence of academic credentials by concerned body;

6) Any higher education institution shall accord academic rank that comply with promotion requirements set by Ministry of Education and the approval shall follow the procedure of promotion;

7) Any higher education institution shall physically avail permanently employed academic staffs or trainers with academic credentials and similar required documents during field visit;

8) Any academic staff shall devote a minimum of 3 hours of consultation each week for the students;

9) weekly teaching load of permanent academic staff shall not exceed 12 credit hours per week and 6 credit hours per week for parttime academic staff. However, the teaching load can exceed up to 15 credit hours per week in exceptional circumstances upon the institutional missions and objectives;

10) Any permanently employed academic staff or trainer shall submit all income tax and pension contribution evidence deducted and paid to the government throughout the employment period;

11) Any academic staff who is permanent employee of one institution shall not become permanent employee of another institution;

12) Any academic staff who is been permanent employee of one institution shall be liable if she or he hired permanently in another institution;

13) Any higher education institutions shall submit the employee contract agreement and consent forms of all academic staff who are permanently employed;

14) Any higher education institution shall hire instructors based on the Ministry of Education

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ሊወስዱ ይገባል

፲) በማንኛውም መርሃግብር እና የትምህርት መስክ ትምህርት የሚያጠናቅቁ ተመራቂ ተማሪዎች ስልጣን ባለው አካል የሚያዘጋጃቸውን የብቃት ማረጋገጫ ፈተና በመውሰድ ወደ ስራ ዓለም ለመቀላቀል የሚያስችላቸውን እውቀትና ክህሎት መላበሳቸውን የሚረጋገጥ ይሆናል።

**<u>፯/ የመምህራን መሰረታዊ ጉዳይ</u>**

፩) ማንኛውም ተቋም ባለስልጣኑ ያወጣውን እና ስርዓተ ትምህርቱ የሚጠይቀውን የመምህራን ወይም የአሰልጣኞች መስፈርት ማሟላት ይኖርበታል፤

፪) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት የሚያስተምር መምህር የትምህርት ደረጃ ከሚያስተምረው ትምህርት አንድ እርከን ወይም ደረጃ ከፍ ማለት ይኖርበታል፤

፫) ማንኛውም ተቋም በቋሚነት የሚቀጥራቸውን መምህራን የትምህርት ማስረጃዎች ትክክለኛነት ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፤

፬) ማንኛውም ተቋም በቋሚነት የተቀጠሩ መምህራን ከተቋሙ ከለቀቁ፣ በለቀቁት ምትክ በሁለት ወር ጊዜ ዉስጥ ቀጥሮ በመተካት ለባለስልጣኑ አስፈላጊዉን መረጃ በማስገባት ማስገምገም እና እንዲያስተምሩ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

፭) ሀገር ዉስጥ ባሉ ተቋማት ማስተማር የሚፈልጉ የወጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው መምህራን ህጋዊ የመኖሪያና የስራ ፈቃድ ያላቸው፣ የትምህርት ማስረጃቸው ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ እንዲሁም አቻ ግመታ የተሰራለት ሊሆን ይገባል፤

፮) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለመምህራን የሚሰጠው የአካዳሚክ ደረጃ ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣውን የአካዳሚክ መምህራን ደረጃ

higher education instructors' nomination standard.

## Part Three

## Application Request for License or Renewal of License And Issuing License, Renewal of License, Cancellation of License or Renewal of License

### 8. *Application for License or Renewal of License*

1) Any institution or program shall request and submit the authority with documents, human resource data and in puts required for license as per the minimum quality standard criteria set by the authority;
2) Any Institution shall pay application fee for issuing of license or renewal of license to the authority;
3) Unless otherwise the institution or program applies before six months for renewal of license, the granted license will be cancelled by the consent of the Institution.
4) Any institution seeking to change its status shall apply to the authority to get license 3 (three) months prior to effecting the anticipated status change;
5) Any institution seeking campus change shall apply to the authority to get license 3 (three) months prior to effecting the anticipated campus change;
6) Any new application request for license of institution or program shall be made based on the schedule the authority notifies.

### 9. *Issuing License*

1) Any higher education institution or program Application request for license shall be granted for three years after fulfilling all the standards set by the Authority.
2) an Institution applying for status change may be accorded the requested status upon fulfilling of the

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

አወሳሰን መስፈርቶች የተከተለ እና በሚዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሰረት ማጽደቅ ይኖርበታል፤

፯) ማንኛውም ተቋም በፈቃድ እና ፈቃድ እድሳት አሰጣጥ ግምገማ ወቅት በቋሚነት የቀጠራቸውን መምህራን ወይም አሰልጣኝ እና የትምህርት ማስረጃዎቹን እና የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ይዞ በአካል መገኘት ይኖርበታል፤

፰) እያንዳንዱ የአካዳሚክ መምህር በሳምንት ቢያንስ 3 ሰአት ድረስ ተማሪዎችን ማማከር ይኖርበታል፣

፱) የቋሚ መምህራን ሳምንታዊ ጫና ከ12 ክሬዲት ሃወር እና የጊዜያዊ መምህራን ከ6 ክሬዲት ሃወር ያልበለጠ ሆኖ እንደ የትምህርት መስኩ በተቋማት ተልዕኮ መሰረት እየታየ እስከ 15 ክሬዲት ሃወር ከፍ ሊል ይችላል፣

፲) ማንኛውም በቋሚነት የተቀጠረ መምህር ወይም አሰልጣኝ በስራ ቆይታው ወቅት ለመንግስት መክፈል ያለበትን የስራ ግብር እና የጡረታ መዋጮ መክፈል እና ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፲፩) በአንድ ተቋም በቋሚነት ተቀጠሮ የሚሰራ ማንኛውም መምህር በሌላ ተቋም በቋሚነት ተቀጥሮ መስራት አይችልም፤

፲፪) ማንኛውም መምህር በቋሚነት ከተቀጠረበት አንድ ተቋም ውጪ በሌላ ተቋም በቋሚነት ተቀጥሮ ቢገኝ በሕግ ሊጠየቅ ይችላል፤

፲፫) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቋሚነት የሚቀጥሯቸው መምህራን ጋር ውል የተዋዋሉበትን ማስረጃ እና መተማመኛ ፎርም ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

፲፬) ማንኛውም ተቋም መምህራንን ሲቀጥር ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው የከፍተኛ ትምህርት የመምህራን መመልመያ መስፈርት መሰረት መሆን ይኖርበታል።

standard set by the authority;

3) Any institution which failed to provide complete documents by the time of document scrutiny shall provide all the unfulfilled documents within 45 (forty-five) days. Where such period lapses, the institution shall be presumed to have unilaterally terminated the license process and it may reapply within 90 (ninety) days by fulfilling all the requirements set by the authority.

4) Any institution whose first license application was denied shall meet all requirements and reapply again within 90 (ninety) days. If the institution fails to reapply within that time frame, it is deemed to have cancelled the license application on its own volition and must resubmit one year after his first application was rejected.

5) Any institution denied license being evaluated pursuant to sub article 4 of this article, may reapply one year after its application for license was denied;

6) Any institution denied license being evaluated pursuant to sub article 5 of this article, may reapply two years after its application for license was denied;

7) Institutions asking for a license for technical and vocational training, short-term trainings, professional competence evaluators, program accreditation service, and consultation services shall be granted a three-year license if they meet standards set by the authority.

8) Any institution requesting application to undertake short term trainings may be granted license for one year where the training spans from one months to six months and two years of license where the training spans from seven months to one year; and license is granted when the institution fulfils the standards set by the authority;

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## ክፍል ሶስት

## የፈቃድ ወይም ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ማመልከቻ ስለማቅረብ

## እና

## ፈቃድ መስጠት፣ ፈቃድ ማደስ፣ ፈቃድ ወይም ፈቃድ እድሳት መሰረዝ

**፲. የፈቃድ ወይም ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ማመልከቻ ስለማቅረብ**

፩) ማንኛውም ተቋም ወይም ፕሮግራም በሚወጣው አነስተኛው የጥራት መለኪያ መስፈርት መሰረት ለፈቃድ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች፣ የሰው ሃይል መረጃዎች እና ግብዓቶች በማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፪) ማንኛውም ተቋም የፈቃድ ወይም የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ለማቅረብ በባለሥልጣኑ የተቀመጠውን የክፍያ ተመን መክፈል ይኖርበታል፤

፫) በባለስልጣኑ ፈቃድ አግኝቶ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ተቋም ወይም ፕሮግራም አገልግሎቱን እየሰጠ ለመቀጠል የፈቃድ ዕድሳቱ ከመጠናቀቁ ስድስት(6) ወራት በፊት የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፤ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ዉስጥ ካልጠየቀ በገዛ ፈቃዱ እንዳቋረጠ ተቆጥሮ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

፬) ማንኛውም ተቋም የደረጃ ስያሜ ለውጥ ከማድረጉ ሶስት(3) ወር በፊት ለባለስልጣኑ የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፭) ማንኛውም ተቋም የትምህርት መስጫ ቦታ ወይም ካምፓስ ለውጥ ቅያሬ ከማድረጉ ሶስት(3) ወር በፊት ለባለስልጣኑ የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፮) ማንኛውም ተቋም አዲስ የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ባለስልጣኑ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ ብቻ ይሆናል፡፡

9) Matters listed out from sub-article 4 through 6 of these articles shall also apply for issues listed out in sub article 7 and 8;

10) The authority may grant license to accreditation association on the basis of fields of studies and on a priority order it deems fit.

**10. *Issuing Renewal of License***

1) Any higher education institution applying for renewal of license shall be granted for five (5) years when the institution fulfills the standards set by the authority;

2) Any Technical and vocational training institution, short term training, professional competence evaluators, program accreditation and consultancy service offering institutions applying for renewal of license shall be granted for three (3) years when the institution fulfills the standards set by the authority;

3) Any institution which failed to provide complete documents by the time of document scrutiny shall provide all the unfulfilled documents within 45 (forty-five) days. Where such period lapses, the institution shall be presumed to have unilaterally terminated the renewal of license process and it may reapply within 90 (ninety) days by fulfilling all the requirements set by the authority.

4) Any institution whose first renewal of license application was denied shall meet all requirements and reapply for a second time within 90 (ninety) days. If the institution fails to reapply within that time frame, it is deemed to have cancelled the renewal of license application on its own volition and must resubmit one year after his first application was rejected.

5) An institution whose application for license renewal made pursuant to sub-article 4 of this

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## ፲. ፈቃድ ስለመስጠት

፩) አዲስ ፈቃድ የሚጠይቅ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወይም ፕሮግራም በባለስልጣኑ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ለሶስት(3) ዓመት የሚቆይ ፈቃድ ይሰጠዋል፤

፪) የደረጃ ስያሜ ለሚጠይቅ ተቋም በባለስልጣኑ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ የጠየቀው የደረጃ ስያሜ ይሰጠዋል፤

፫) በሰነድ ምርመራ ወቅት ሰነድ ያጓደለ ተቋም በአርባ አምስት (45) ቀናት ውስጥ አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል። የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለፈ በገዛ ፈቃዱ የፈቃድ ሂደቱን እንዳቋረጠ ተቆጥሮ፣ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን መመዘኛዎች በማሟላት በድጋሚ ሊያመለክት ይችላል።

፬) ለመጀመሪያ ጊዜ ፈቃድ የተከለከለ ተቋም ክልከላው ከተገለፀበት ቀን አንስቶ በ90 ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን መመዘኛዎች በማሟላት በድጋሚ ሊያመለክት ይችላል። የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለፈ ተቋሙ በገዛ ፈቃዱ የፈቃድ ሂደቱን እንዳቋረጠ ተቆጥሮ ከአንድ አመት በኃላ እንደ አዲስ ሊያመለክት ይችላል፣

፭) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ተገምግሞ ፈቃድ በድጋሚ የተከለከለ ተቋም ፈቃድ ከተከለከለበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ በድጋሚ እንደ አዲስ ሊያመለክት ይችላል፤

፮) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ከአንድ ዓመት በኋላ የፈቃድ ጥያቄ አቅርቦ ፈቃድ የተከለከለ ተቋም ከተከለከለበት ጊዜ ጀምሮ ከሁለት ዓመት በኃላ በድጋሚ እንደ አዲስ ሊያመለክት ይችላል፤

፯) የቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ የአጫጭር ስልጠና፣ የሙያ ምዘና፣ የፕሮግራም እውቅና እና

article is denied, it shall transfer students to another institution having a license with specific program and report to the authority with in 1 month;

6) An institution that has been denied renewal of a license or ordered to transfer students to institutions having a license may re-apply for a new license after two years following the announcement;

7) When the authority face difficulties to have a field visit evaluation of institutions seeking to have renewal of license, evaluation may be made by though current technology or other feasible means which don't compromise the standard sets and granted provisional certificate.

### 11. *Cancellation of License or Renewal of License*

1) The authority may cancel the license of any institution, if it fails to apply renewed of license on time;

2) The license or renewal of license of an institution or a program may be cancelled where the institution is proven through evaluation to have compromised some of the criteria set by the authority;

3) unless otherwise the foreign higher education institution renewed its accreditation, the authority shall cancel the host country institution license granted for the modality and specific program.

4) Unless otherwise the institution makes improvements on compromised quality of education, legal violation and the imposed penalty, the authority shall cancel the institution or program license.

### 12. *Exit procedure of an Institution or a Program*

1) Any institution which seeks, out of its own self initiation, to close the program or training to

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የፈቃድ ጥያቄ ያቀረበ ተቋም ባለስልጣኑ የሚያወጣውን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ የሶስት ዓመት ፈቃድ ይሰጠዋል፤

፰) ማንኛውም አጫጭር ስልጠና ለመስጠት የፈቃድ ጥያቄ ያቀረበ ተቋም ባለስልጣኑ የሚያወጣውን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ከአንድ እስከ ስድስት ወር ስልጠና ለሚሰጥ የአንድ ዓመት ፈቃድ እንዲሁም ከሰባት ወር እስከ አንድ ዓመት ስልጠና ለሚሰጥ የሁለት ዓመት ፈቃድ ይሰጠዋል፤

፱) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እስከ 6 የተጠቀሱትን ጉዳዮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 ለተዘረዘሩትም ተግባራዊ ይሆናሉ፤

፲) ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እውቅና ለሚሰጡ የሙያ ማህበራት ፈቃድ ሲሰጥ የትምህርት መስኮችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በቅደም ተከተል ሊሆን ይችላል።

## ፲. ፈቃድ ማደስ

፩) የፈቃድ እድሳት ያቀረበ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወይም ፕሮግራም በባለስልጣኑ የተቀመጡትን የፈቃድ እድሳት መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ለአምስት (5) ዓመት ፈቃዱ ይታደስለታል፤

፪) የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ያቀረበ ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም፣ የአጫጭር ስልጠና፣ የሙያ ምዘና፣ የፕሮግራም እውቅና እና የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በባለስልጣኑ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ ባለስልጣኑ ለሶስት (3) ዓመት ፈቃዱን ያድስላቸዋል፤

፫) በሰነድ ምርመራ ወቅት ሰነድ ያጓደለ ተቋም በአርባ አምስት (45) ቀናት ውስጥ አሟልቶ

which license was granted from the authority or due to acceptable force measure which prevented it from sustaining its activities may only close such program or training by applying for the authority before 6 months and meets the criteria the authority has set for such action;

2) Any institution shall not admit new students for a program to which a willful closing application has been submitted to the authority, from the moment such application has been made;

3) For the application indicated on sub-article 1 of this article, the institution shall transfer the students to another licensed institution on its own cost and shall report the task for the authority within time frame to be decided by the authority. If the institution fails to take such action, sufficient amount of money shall be deducted from the five hundred thousand birr the institution had blocked at bank for such purposes. The institution shall reimburse the money which has been deducted from the guarantee attached.

4) Notwithstanding the provisions of sub-article 3 of this article, an institution whose request to close has been accepted may be specially ordered to take proper action without compromising quality of education to train and graduate students whose field of studies are not offered by other institutions in the town the closing campus is situated or in the nearby locality;

5) An institution that is ordered to close programs or training due to compromising quality education or violating the law shall transfer students to another licensed institution

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

ማቅረብ ይኖርበታል። የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለፈ ተቋሙ በገዛ ፈቃዱ የፈቃድ እድሳት ሂደቱን እንዳቋረጠ ተቆጥሮ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን መመዘኛዎች በማሟላት በድጋሚ ሊያመለክት ይችላል።

፱) የፈቃድ እድሳት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከለከለ ማንኛውም ተቋም ወይም ፕሮግራም በባለስልጣኑ የተገለፁትን የተጓደሉ መመዘኛዎች አሟልቶ በዘጠና (90) ቀናት ዉስጥ እንደገና ሊያመለክት ይችላል። የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለፈ ተቋሙ በገዛ ፈቃዱ የፈቃድ እድሳት ሂደቱ እንዳቋረጠ ተቆጥሮ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ በተቀመጠው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

፲) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት አመልክቶ የፈቃድ እድሳት የተከለከለ ተቋም የተቀበላቸውን ተማሪዎች በትምህርት መስኩ ፈቃድ ወዳለው ሌላ ተቋም ተዛውረው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ወይም እንዲማሩ በማድረግ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበታል፤

፲፩) የፈቃድ እድሳት የተከለከለ ወይም ተማሪ አዛውር የተባለ ተቋም ዉሳኔው ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ በተከለከለበት የትምህርት መስክ ከሁለት ዓመት በኋላ በድጋሚ እንደ አዲስ ሊያመለክት ይችላል፤

፲፪) ተቋማት ላቀረቡት የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ባለስልጣኑ በአካል ተገኝቶ መገምገም የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር ወቅቱ በፈቀደው ቴክኖሎጂ አማካኝነት ወይም በሌሎች አማራጮች መስፈርቱን በማያጓድል ሁኔታ ሊገመገም እና ጊዜያዊ የፈቃድ ሰርተፊኬት ሊሰጥ ይችላል።

of their choice by covering the entire cost within the time frame decided by the authority and report the action to the authority. If it fails to do so, a sum of money sufficient for this action may be deducted from the five hundred thousand (500.000) birrs blocked at a bank as a guarantee.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 13. *About Making Suggestion*

1) If any person or institution know or observe any means concerning violation declared in this directive, the violation shall be reported to the authority. The authority shall take corrective measures as per the institutional procedural directive.
2) The authority has a duty to protect and confidentiality of the whistle blower.

### 14. *Legal Violations*

1) Notwithstanding responsibility being taken by the institution and the trainees thereto, an institution which has been found to undertake education and training without getting license from the authority shall be subjected to civil and criminal liability;
2) Any violation committed by any institution declared by this directive shall be subjected to civil and criminal liability.

### 15. *Accountability and Responsibility*

1) Any institution violates the higher education proclamation, technical and vocation training proclamation, council of minister's regulation for education and training authority structure, power and responsibilities, other directives of the authority and evaluation standards shall

## ፲፭. ፈቃድ ወይም ፈቃድ እድሳት መሰረዝ

፩) ፈቃድ አግኝቶ ሲሰራ የቆየ ማንኛውም ተቋም የፈቃድ እድሳት በወቅቱ ካልጠየቀ ባለስልጣኑ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፣

፪) ማንኛውም ተቋም ወይም ፕሮግራም በባለስልጣኑ የተቀመጡ መስፈርቶችን አጓድሎ ሲገኝ እና በግምገማ ሲረጋገጥ የተሰጠው ፈቃድ ወይም ፈቃድ እድሳት ይሰረዛል፡

፫) ማንኛዉም በድንበር ተሻጋሪ ትምህርት መርሃ-ግብር የሚያስተምር የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በዉጭ ሀገር ያለዉ ተቋም እዉቅናዉ ካልታደሰ በሀገር ዉስጥ ያለዉ ተቋም የመርሃ ግብሩ እና የትምህርት መስኩ ፈቃዱ ይሰረዛል፤

፬) ማንኛውም ተቋም ወይም ፕሮግራም የትምህርት ጥራትን ካጓደለ፣ የከፍተኛ ትምህርት አሰጣጥ ህጎችን ከጣሰ እና የእግድ ቅጣት ተላልፎበት ካላሻሻለ በባለስልጣኑ የሰጠውን ፈቃዱ ይሰረዛል፤

## ፲፮. የተቋም ወይም የፕሮግራም የመውጫ አሰራር ስርዓት

፩) ማንኛውም ተቋም በራሱ ተነሳሽነት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ያገኘበትን ፕሮግራም ወይም ስልጠና መዝጋት የሚችለው ተቀባይነት ባለው መነሻ ምክንያት መማር ማስተማሩን ማስቀጠል በማይችልበት ሁኔታ ለባለስልጣኑ ከ6 ወር በፊት በማመልከት ባለስልጣኑ ያወጣውን ዝርዝር መስፈርት ካሟላ እና ሲፈቀድለት ብቻ ሊወጣ ይችላል፤

፪) ማንኛውም ተቋም ፈቃድ ያገኘበትን ፕሮግራም

be legally liable and responsible.

2) The authority shall keep confidential all the information collected from institutions in the process of administration and implementation of this directive.

## *16. Duty to Cooperate*

1) Institutions are duty bound to provide the authority any information and evidences it needs at any time. This shall be done as per the procedure which will be prepared to designate the duties and responsibilities of the two parties;
2) The authority has the duty to provide important information pertaining to licensing to higher education institutions and technical and vocational training institutions.

## 17. *Grievance and Resolution Procedure*

Any institution aggrieved with the actions and decisions of the licensing entity may file its grievance to the authority based on provisions of this directive;

## *18. Inapplicable Laws*

1) Directives promulgated by the Ministry of Education namely: Recognition, License and Renewal Directives, Undergraduate Directive No. 575/2021, Distance Education Directive No. 576/2021, cross border Education Directive No. 578/2021, Online Learning Directive No. 806/2021, Postgraduate Directive No. 574/2021 and Institutions' Status Directive No. 577/2021 will be applicable unless it's contents are against this directive;
2) The Technical and Vocational Education and Training Institutions Program Registration and Accreditation Directive promulgated will be applicable unless it's contents are against this directive;
3) Notwithstanding provisions of sub-article 1 and

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education

ወይም ስልጠና መስክ በራሱ ተንሳሳሽነት ለመዝጋት ጥያቄ ለባለስልጣኑ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በፕሮግራሙ አዳዲስ ተማሪዎችን መቀበል አይችልም፤

፫) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለቀረበው ጥያቄ በባለስልጣኑ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ ተማሪዎችን ፈቃድ ወዳለው ተቋም በማዘዋወር እና የሂደቱን ሙሉ ወጪ በመሸፈን ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል። ይህንን ማድረግ ካልቻለ በባንክ ካስያዘው አምስት መቶ ሺ ብር (500000) ላይ ለዚሁ አላማ እንዲውል ይደረጋል። ተቋሙ ለሌሎች ቀሪ ካምፓሶች ወይም የትምህርት መስኮች ወጪ የተደረገውን ማስያዣ መተካት ይኖርበታል፤

፬) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ያቀረበው ጥያቄ በባለስልጣኑ ተቀባይነት ያገኘ ተቋም የሚዘጋው ፕሮግራም(ሞች) ካምፓሱ በሚገኝበት ከተማ በሌሎች ተቋማት የማይሰጥ ከሆነ በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን ጥራቱ ባልተጓደለ አኳኋን አስተምሮ እንዲያስጨርስ ወይም እንዲያስመረቅ ሊወሰን ይችላል፤

፭) በጥራት መጓደል ወይም በህግ ጥሰት ምክንያት ፈቃድ ያገኘበትን ወይም ያገኘባቸውን ፕሮግራም(ሞች) ወይም ስልጠና(ዎች) እንዲዘጋ በባለስልጣኑ የታዘዘ ተቋም እየተማሩ ያሉ ተማሪዎችን ፈቃድ ወዳለው ሌላ ተቋም ተማሪዎቹ በመረጡት እና በባለስልጣኑ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ በማዘዋወር እና የሂደቱን ሙሉ ወጪ በመሸፈን ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል። ይህንን ማድረግ ካልቻለ በባንክ ካስያዘው አምስት መቶ ሺ ብር ላይ ለዚሁ አላማ እንዲውል ይደረጋል።

2 of this article, standards set based on the directive are also repealed by this directive;

4) Any directive, administrative decision, or customary practice shall not be applicable for matters contrary to the things mentioned in this directive.

***19. Amendment***

Ministry of Education may amend this directive when it is necessary.

**20. *Effective date of the directive***

This directive shall have effect as of the date of its registration with ministry of junstice and its uploading on the official website of Ministry of Education.

**Addis Ababa 2024**

**Birhanu Nega (Professor)**
**Minister, Ministry of Education of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፫. ጥቆማ ስለማቅረብ

፩) ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱ ድንጋጌዎችን የሚጻረር ጥፋት መፈጸሙን በማንኛውም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል። ባለስልጣኑ ለሚቀርብለት ጥቆማ የሚያስተናግድበትን ስርዓት በመዘርጋት በተቋማት የስነ ስርዓት መመሪያ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፪) ባለስልጣኑ የጥቆማ አቅራቢውን ሚስጥራዊነትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ ይኖርበታል።

### ፲፬. ህግ ስለመተላለፍ

፩) ከፈቃድ ሰጪው አካል ምንም ዓይነት የትምህርትና ስልጠና ፈቃድ ሳያገኝ ትምህርት ወይም ስልጠና ሲሰጥ የተገኘ ተቋም ሙሉ ኃላፊነቱን ተቋሙ እና ሰልጣኞች የሚወስዱ ሆነው ተቋሙ ላጠፋው ጥፋት ፈቃድ ሰጪው አካል ተቋሙን አግባብነት ባለው ህግ ሊጠየቅ ይችላል፤

፪) ማንኛውም ተቋም በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተጠቀሱ ማናቸውንም ጉዳዮች ተላልፎ ቢገኝ ህግ እንደመተላለፍ ተቆጥሮ ፈቃድ ሰጪው አካል ተቋሙን አግባብነት ባላቸው ህጎች ሊጠየቅ ይችላል።

### ፲፭. ስለ ተጠያቂነት እና ህላፊነት

፩) ማንኛውም ተቋም በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ፣ በቴክኒክ እና ስልጠና አዋጅ፣ በባለስልጣኑ የአደረጃጀት ስልጣን እና ተግባር መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ፣ ሌሎች የባለስልጣኑ መመሪያዎች እና የመገምገሚያ መስፈርቶች ተላልፎ ሲገኝ እንደ የህግ ጥሰቱ ተጠያቂ ወይም ሃፊነት ሊኖረው ይችላል፤

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

፪) ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ በማስተዳደር እና በማስፈፀም ሂደት ከተቋማት የሚሰበሰበውን መረጃ ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ ይኖርበታል፤

**፲፮. የመተባበር ግዴታ**

፩) ተቋማት ባለስልጣኑ በማንኛውም ጊዜ የሚፈልገውንና የሚጠይቀውን መረጃና ማስረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው። ይህም የሁለቱም አካላት ተግባር እና ሃላፊነትን በተመለከተ በሚዘጋጀው የአሰራር ስርዓት መሰረት ይሆናል፤

፪) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ ዙሪያ በከፍተኛ ትምህርት እና በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ የሚሰማሩ ወይም ለተሰማሩ ተቋማት ስለፈቃድ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የመስጠት ግዴታ ይኖርበታል።

**፲፯. ቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት**

በዚህ መመሪያ መሰረት ፈቃድ ሰጪው አካል በሚሰጣቸው ማናቸውም ዉሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ተቋም ለባለስልጣኑ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤

**፲፰. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

፩) ከዚህ በፊት በትምህርት ሚኒስቴር የወጡ የእውቅና ፈቃድ እና እድሳት መመሪያዎች፣ የመደበኛ የመጀመሪያ ዲግሪ መመሪያ ቁጥር 575/2013፣ የርቀት ትምህርት መመሪያ ቁጥር 576/2013፣ የድንበር ተሻጋሪ መመሪያ ቁጥር 578/2013፣ የበይነ መረብ መመሪያ ቁጥር 806/2013፣ የድህረ ምረቃ መመሪያ ቁጥር 574/2013፣ የተቋማት የደረጃ ስያሜ መመሪያ ቁጥር 577/2013፣ ከዚህ መመሪያ ጋር እስካልተቃረኑ ጊዜ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፪) ከዚህ በፊት በ2003 በትምህርት ሚኒስቴር ወጥቶ ሲሰራበት የነበረው የቴክኒክና ሙያ

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

ትምህርት እና ስልጠና ተቋማት የፕሮግራም ምዝገባ እና የእውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ከዚህ መመሪያ ጋር ካልተቃረነ ጊዜ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖራዋል፡፡

፫) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ መመሪያውን ተከትሎ የወጡ መስፈርቶችም በዚህ መመሪያ መሰረት ተሸረዋል፤

፬) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ የአስተዳደር ውሳኔ፣ የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**፲፱. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህን መመሪያ ትምህርት ሚኒስቴር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል።

**፳. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትምህርት ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ 2016 ዓ.ም**

**ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር**

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education
በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር